# Moral Education, 2018 EC, Grade 6 model exam

Grade 6 · Moral Education · 2018 E.C.

**Time allowed:** 120 minutes **Questions:** 36 **Total marks:** 36

Name ______________________ Grade ________ ID No. ________ Date ________

**1.** ግብረገባዊ ውሳኔዎችን ለመወሰን የሌሎችን ሰዎች አስተያየትና ይሁታን አለመጠየቅ ምንን ይገልጻል? (1)

A. በራስ መተማመን
B. ለሌሎች ማሰብ
C. ድፍረት
D. ኢ- ተለዋዋጭ

**2.** ውስጣዊ እሳቤያችን ከውጫዊ ድርጊታችን ጋር መጣጣሙን የሚገልፅ ሀሳብ የቱ ነው ? (1)

A. ተጠያቂነት
B. ልዩነት
C. መቻቻል
D. ምሉዕነት

**3.** በኢትዮጵያውያን መካከል የሚገኙ የግብረ ገብ እሴቶች ውስጥ ምሳሌ የማይሆነው የቱ ነው? (1)

A. ታላላቆችን ማክበር
B. ስርአት አልበኝነት
C. እንግዳ ተቀባይነት
D. ስጦታን በሁለት እጅ መቀበል

**4.** በቤተሰብ ሆነ በማህበረሰብ ውስጥ በስምምነት ለመኖር እያንዳዱ ሰው የሚጠበቅበትን ሀላፊነት በአግባቡ መወጣት የየትኛውን የሃላፊነት አይነት ነው? (1)

A. የግለሰብ ሀላፊነት
B. የቤተሰብ እና የማህበረሰብ
C. ሀገራዊ ሀላፊነት
D. ቃልን መጠበቅ

**5.** ከሚከተለት ውስጥ የግብረ ገብ ምለዕነት ጠቀሜታን የሚያሳየው የቱ ነው? (1)

A. ማህበራዊ ችግሮችን ሉ መፍታት ያስችሊሌ
B. ማህበራዊ ችግሮችን ያሰፋል
C. ማህበራዊ ግንኙነቶችን ያጠፋል
D. በማህበረሰብ ዘንዴ ተቀባይነትን ያሳጣል

**6.** ከሚከተሉት ውስጥ የአንድ ሰው ጠንካራ የስራ ባህል መገለጫ የሆነው የቱ ነው? (1)

A. የስራ ሠዓትን ማክበር እና ሁሉንም ሥራ ለብቻ መሥራት
B. የተሰጠንን ስራ እንደነገሩ አጠናቆ በወቅቱ እና በአግባቡ ማስረከብ
C. የማያደክሙ ስራዎችን መምረጥ እና እነሱ ላይ ትኩረት ማድረግ
D. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶችን እና እውቀት በመማር መሥራት

**7.** ከሚከተሉት ባህሪያት ውስጥ የታታሪ ተማሪዎች መገለጫ ከሆኑት ውስጥ የሚካተተው የቱ ነው? (1)

A. በጋራ ሰርቶ ለብቻ ሁሉንም ጥቅም መውሰድ
B. ለፈተናዎች አለመዘጋጀት ፣ከጓደኛ መኮረጅ
C. አብዝቶ እንቅልፍ መውደድ፣ በጥዋት አለመነሳት
D. ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ያሉ መፅሐፍትን ማንበብ

**8.** ከሚከተሉት ውስጥ የግብረገብ ምሉዕነት ያላቸው ተማሪዎች መገለጫ የሆነው የቱ ነው? (1)

A. በህብረተሰቡ ዘንድ ይናቃሉ
B. ማንኛውም ጫና ለመቋቋም ብቃት አላቸው
C. ከህብረተሰቡ የተገለሉ ናቸው
D. ሁሉም መልስ ናቸው

**9.** በግብረገብ ምሉዕነት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ከሚፈፅሙት ተግባራቶች የማይካተት አንዱ __________ነው። (1)

A. የማያውቁት ነገር ሲገጥማቸው አይናገሩም
B. ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ሀቀኛ ናቸው
C. ማንኛውንም ነገር ለማስመሰል አይሞክሩም
D. የሌሎችን ሰዎች ሚስጥር ይጠብቃሉ

10. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ግብረገብ ምሉዕነት ትክክል የሆነው የቱ ነው? (1)

A. አንድ ሰው ስለ ነገሮች ባለው ግለዊ እምነት ተለዋዋጭ አቋምን ማሳየት

B. አንድ ሰው በሚፈፅማቸው ድርጊቶች መካከል እና ግላዊ እምነት ልዩነት መኖር

C. አንድ ሰው ስለነገሮች ባለው ግላዊ እምነት ኢ-ተለዋወጭ አቋምን ማሳየት

D. አንድ ሰው በስነ ምግባሩ መጥፎ መሆን

11. ገንዘብ፣ ሽልማት፣ ስጦታና አድናቆት ሳይጠብቁ በነፃ የሚፈፀም ተግባር _________ ይባላል (1)

A. የጉልበት ስራ

B. ስራ ፈጠራ

C. በጎ አድራጎት

D. የሀብት ክምችት

12. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ህይወታችንን በምሉዕነት ለመምራት ከሚያስፈልጉ ነገሮች መካከል አይካተትም (1)

A. ሀቀኛ መሆን

B. ውሸት መናገር

C. በራስ መተማመን

D. ሚስጥር መጠበቅ

13. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረገብ ምሉዕነት ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው? (1)

A. በቀላሉ የገቡትን ቃል የሚያፈርሱ ግለሰቦች መበራከት

B. ችግሮችን በብቃት የመፍታት አቅምን ይቀንሳል

C. መጥፎ ተግባራትን የሚያጋልጡ ግለሰቦች ማነስ

D. በራሳቸው የሚተማመኑ ጠንካራ የስራ ባህል ያለው ማህበረሰብ ይፈጠራል

14. ምሉዕነት ያላቸው ግለሰቦች ከሚኖራቸው መሰረታዊ እምነቶች መካከል የማይካተተው የትኛው ነው? (1)

A. ተጠያቂነት

B. ተለዋዋጭ

C. ድፍረት

D. ርህራሄ

15. አንድ ሰው ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ነገር እንዲተገብር የሚያደርግ ውስጣዊ ችሎታ ምን ይባላል? (1)

A. ታማኝነት

B. ድፍረት

C. ሀላፊነት መወጣት

D. ተጠያቂነት

16. አጭበርባሪነትን እና ሌብነትን ማስወገድ መቻል ከሚከተሉት የትኛውን ይገልጻል? (1)

A. ተጠያቂነት

B. ሀቀኝነት

C. ታማኝነት

D. ምሉዕነት

17. የንባብ ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው? (1)

A. እውቀትን ያሰፋል

B. የቋንቋ አጠቃቀም ክህሎትን ያዳብራል

C. ጭንቀት ይቀንሳል

D. ሁሉም መልስ ናቸው

18. ከመልካም ባህሪ ማሳደጊያ ወይም ማዳበሪያ መንገዶች መካከል የሚመደበው የትኛው ነው? (1)

A. ለሕግ ተገዥ መሆን

B. የትምህርት ቤት ህግና ደንብ ማክበር

C. ራስን መቆጣጠር

D. ሁሉም

19. ስለ ህግ ትክክል የሆነው የትኛው ነው ? (1)

A. ህግ የአንድ ሀገር መተዳደሪያ ነው

B. ህግ ሲወጣ ለተወሰነ ጊዜ ነው

C. ህግ የሚወጣው ሰዎችን ለማበላለጥ ነው

D. ህጎች የሰዎችን መብት ይጥሳሉ

20. በአንድ ሀገር ውስጥ የትኛውም ህግ ማሟላት ካለበት መስፈርቶች ውስጥ የሚካተተው የቱ ነው? (1)

A. ተለዋጭነት

B. ቋሚነት

C. ወጥነት

D. ሁሉም

**21.** ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ግብር ስወራ ተጽዕኖ ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው? (1)

**A.** መንግስት መሰብሰብ የሚችለውን ገቢ እንዲቀንስ ያደርጋል

**B.** መንግስት ለዜጎች የሚያቀርበውን አገልግሎት እንዲቀንስ ያደርጋል

**C.** ግብር ስወራ በሀገር ላይ እንጂ በግለሰብ ህይወት ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም

**D.** መሰብሰብ ያለበት ገቢ ባለመሰብሰቡ የልማቶች ስራዎች እንዳይሰሩ ያደርጋል

**22.** አንድ ሀገር ታታሪ ዜጎች እነዲኖሩዋትና በኢኮኖሚ እንድታድግ ጠንካራ የስራ ባህልን ከየት ጀምራ ማስተማር አለባት? (1)

**A.** ዜጎች ስራ ሲቀጠሩ

**B.** ከተማሪነት ጊዜ ጀምሮ

**C.** በጎልማስነት እድሜ ላይ

**D.** ዜጎች ከሀገር ሊወጡ ሲፈልጉ

**23.** ከሚከተሉት መካከል ከጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ ራስን ማስተዳደርን የሚገልፅ ሀሳብ የትኛው ነው? (1)

**A.** የህግ ተገዥነት

**B.** ሉዓላዊነት

**C.** የህግ ከለላ

**D.** ህገ መንግስት

**24.** ከሚከተሉት መካከል ግብር ስወራ ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው? (1)

**A.** ገቢን አሳንሶ ማቅረብ

**B.** የተጋነነ ወጪ

**C.** መረጃን በአግባቡ ማደራጀት

**D.** ሀሰተኛ የግብር ሰነድ

**25.** ህገ- ወጥ የህፃናት ዝውውር ልጆች ላይ የሚያስከትለው ችግር ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው? (1)

**A.** ህይወታቸውን በመጥፎ ሁኔታ እንዲመሩ ያደርጋቸዋል

**B.** የቤተሰብ ፍቅር የማግኘት መብታቸውን ያጣሉ

**C.** መሰረታዊ ፍላጎታቸው የማግኘት መብት ይከበርላቸዋል

**D.** ለአካላዊ እና ስነ- ልቦናዊ ችግሮች ይጋለጣሉ

**26.** የሰውነታችን ጤና እንዳይቃወስና ጉዳት እንዳያጋጥመው ተገቢውን ትኩረትና እንክብካቤ መስጠትን የሚያመለክተው የቱ ነው? (1)

**A.** ለአካላዊ ሰውነት ክብር መስጠት

**B.** ለአስተሳሰብ ክብር መስጠት

**C.** ለጤና ክብር መስጠት

**D.** ለጓደኛ ክብር መስጠት

**27.** ከሚከተለት ውስጥ ከመልካም ባህሪ ምሳሌዎች የማይካተተው የቱ ነው? (1)

**A.** ትሁት መሆን

**B.** ስህተትን አለመቀበል

**C.** ጥሩ ጓደኛ መምረጥ

**D.** ፍቃድ መጠየቅ

**28.** ራስን መቆጣጠር (መግዛት) ሲባል ............ማለት ነው? (1)

**A.** ስሜትንና ምኞትን መግታት

**B.** በራስ ላይ ማዕቀብ መጣል

**C.** ራስን መጣል

**D.** ንብረት መቆጣጠር

**29.** ከሚከተሉት ውስጥ መልካም ባህሪን አለመላበስ ከሚያስከትላቸው አሉታዊ ውጤቶች መካከል የሚመደበው የትኛው ነው? (1)

**A.** ከስሕተት መማር

**B.** የትምህርት ቤት ንብረት መውደም

**C.** ራስን መቻል

**D.** አመስጋኝ መሆን

**30.** ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ የሚያገኙት መሰረታዊ መብት ነው (1)

**A.** ዲሞክራሲያዊ መብት

**B.** የደህንነት መብት

**C.** ሰብዓዊ መብት

**D.** የሴቶች መብት

**31.** መንግስት ከህዝቦችና ከተቋማት ገንዘብ በመሰብሰብ የማሕበረሰቡን የልማት ጥያቄ የሚመለስበት መንገድ ይባላል። (1)

**A.** የግብር ሰነድ

**B.** ግብር ስወራ

**C.** ግብር

**D.** የተጋነነ ወጪ

**32.** ስልጣንን አለአግባብ በመጠቀም እና ለቤተሰብ ወይም ለወዳጅ ያልተገባ ጥቅም በመስጠት የሚከናወን የሙስና ወንጀል አፈፃም ይባላል። (1)

A. ሐሰተኛ የግብር ሰነድ
B. ወገንተኝነት
C. ግብር ስወራ
D. ጉቦ መስጠት

**33.** ህግን ለማክበር ወይም ላለመጣስ የሚደረግ እንቅስቃሴ ምን ይባላል? (1)

A. ሕገ-መንግስት
B. የሕግ የበላይነት
C. ለሕግ ተገዥነት
D. መልስ የለም

**34.** ለሕግ ተገዥነት ወይም ለሕግ መገዛት ከሚያስገኘው ጠቀሜታ መካከል የማይመደበው የትኛው ነው? (1)

A. የስልጣን ገደብ መኖር
B. ፍትሐዊ የሐብት ክፍፍል
C. ሙስናን ለመዋጋት
D. የመብቶች ጥሰት

**35.** ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ማለት ነው (1)

A. ማዳላት ያለበት መሆን አለባት
B. ለረዥም ጊዜ መቆየት አለበት
C. የማንኛው ሀገር ዜጋ መብት ነው
D. የጥቂት ግለሰቦች ዜጎች መብት ነው

**36.** ማለት ገንዘብን ፣ጊዜንና ንብረትን በአግባቡ መጠቀምና ለቀጣይ ፍጆታ ማቆየት ነዉ (1)

A. ንብረት
B. ቁጠባ
C. ኢኮኖሚ
D. መዝናናት

— END OF EXAMINATION —